
# <u>እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

በጃንዋሪ የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ላይ የተስተዋለ ቢሆንም፤ ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የደመና መጨመርና መስፋፋት እንዲሁም የነበረው ቅዝቃዜ በአብዘኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀንሶ ተስተውሏል። በዚህም መሠረት በጥቂት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሰሜናዊው ክፍል፣ የደቡብ ትግራይ፣ ከኦሮሚያ ጅማ አካባቢ፣ የምሥራቅ አማራ እና የደቡብ አፋር አካባቢዎች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው። በሌላ በኩል የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በማይጨው 4.0፣ በመሀል ሜዳ 2.2፣ በሾላ ገበያ 4.0፣ በወገል ጤና 1.4፣ በደብረዝይት 1.3፣ በሮቤ 4.0፣ በአዲስ አበባ ቦሌ ኢንጂነሪንግ 3.6፣ በአደሌ 3.0፣ በአዴት 5.0፣ በአዲግራት 1.0፣ በሀሮማያ 0.0፣ በአምባማርያም 3.5፣ በአርሲ ሮቤ 2.5፣ በአፀቢ 3.5፣ በደብረብርሃን 1.0፣ በዳንግላ 3.5፣ እንዲሁም በደባርቅ 4.5፣ በዲግሪ ሴልሽየስ የሚጠቀሱ ናቸው።


በአሥሩ ቀናት ውስጥ የዘነበው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-39 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፤ ከደቡብ ብብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የአማን፣ ከጋምቤላ የማሻ እንዲሁም ከኦሮሚያ የጨራ ጣቢያዎች ላይ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፣ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች በደረቅ የአየር ሁኔታ ስር እንደቆዩ ከአየር ሁኔታ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1 እና 2 )።

በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ጥቂት የደቡብ ትግራይ፣ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ኪስ ቦታዎች፤ ከአፋር የአሳይታ ጣቢያ አካባቢ፣ ከደቡብ ብብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ ምስራቃዊው ክፍል፤ ከኦሮሚያ የጂማ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)።


ካርታ1   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1- 10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

በጃንዋሪ የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብስባ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የታየው የደመና መጨመርና መስፋፋት ሁኔታ ለቋሚ ተክሎችና ለእንስሳት መኖ አቅርቦት አመቺ ከመሆኑ በተጨማሪ የቅዝቃዜው ሁኔታ በአብዘኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀንሶ መታየቱ በእንስሳትና በቋሚ ተክሎች ላይ የነበረውን አሉታዊ ጎን እንዲቀንስ አድርጎታል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጥቂት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሰሜናዊው ክፍል፣ ከኦሮሚያ በጅማ አካባቢ፣ የደቡብ ትግራይ፣ የምሥራቅ አማራ እና የደቡብ አፋር በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ የተመዘገበው አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ለእንሰሳት መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለበልግ እርሻ ማሳ ዝግጅት ምቹ ሁኔታዎችን ፍጥሯል።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2018 የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ጃንዋሪ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ ከፊል ደረቅና መጠነኛ እርጥበት በደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ እንዲሁም መጠነኛ እርጥበት በታችኛው አዋሽ ተፋሰስ ላይ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የአገሪቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ተስተዉሎባቸው እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2018 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ አመዝኖ ይቆያል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ ሥፍራዎች ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ከመጠበቁ በስተቀር በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሰረት በመጪዎቹ አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ኢሉአባቦራ እና ጅማ፣ አዲስ አበባ፣ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ከትግራይ  የደቡብ ዞኖች እንዲሁም ከአፋር የዞን 3 እና 5 አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በአንጻሩ የሌሊቱና የማለደው ቅዝቃዜ በአብዛኛው እየቀነሰ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

# እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

# በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ሁለተኛው የጃንዋሪ አስር ቀናት በአመዛኙ ከሚስተዋለው ደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው መኸር አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚከናወኑበት ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ በሂደት ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡ በተሰጠው የአስር ቀናት የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የጃንዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት በተወሰነ ደረጃ ከሚጠናከሩ እርጥበት አዘል የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተነሳ በጥቂት የኦሮሚያ፣ የምስራቅ አማራ፣ የደቡብ ትግራይና የአፋር አንዳንድ ዞኖች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ሰብሎች ሙሉ በሙሉ በተሰበሰቡበትና የበልግ ወቅት ዝግጅትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል አንፃር በጎ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው የእርጥበት መጨመር በትንበያው ላይ ለተጠቀሱት የአርብቶ አደር አካባቢዎች የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜንም ሆነ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የሰብል ስብሰባው ሙሉ በሙሉ ባልተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች የሚጠበቀው ዝናብ ጉዳት ሊያደርስ

ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ አስቀድመው እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላ መልኩ ከከባቢ ዓየር እርጥበትና ከደመና መጨመር ጋር ተያይዞ በባለፉት ጥቂት ወራት የተስተዋለው ጠንከር ያለ የሌሊትና የማለዳ ቅዝቃዜ እንደሚቀንስ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች ጤናማ እድገት እንዲሁም ለእንስሳት ስምሪት በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ደረቅ ሆነው በሚቆዩ አካባቢዎች አርሶ አደሮች የሰብል ስብሰባና ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን ተጨማሪ እድል የሚያገኙ በመሆኑ ይህንኑ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ያለመዘናጋት የሰብል ስብሰባንም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን በተቻለ ፍጥነት እንዲያከናውኑ ይመከራሉ፡፡

## እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመእኖ የሚቆይ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ስምጥ ሸለቆና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካካለኛውና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለጥቂት ቀናት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ ስንመለከት በአንዳንድ የሪፍት ቫሊ፣ የአፋር ደናክል፣ የአዋሽ፣ የባሮ አኮቦ እና በጥቂት የኦጋደን ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የሆነ የዝናብ መጠን ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለአነስተኛ ወንዞች መጠነኛ አስተዋፆ ይኖረዋል፡፡